# የ"ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" እና የአጫፋሪዎቹ የእብደት ሴራ

*መኮንን መንግስቱ*

09-04-14

በቅርቡ "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" የተሰኘው ተቋም እንዲሁም አጫፋሪዎቹ "የቱርካና ሃይቅ ወዳጆች" እና "ሪፍት ቫሊ" የሚባሉ ድርጅቶች ቀደም ሲል የምናውቀውን የሻገተና የእብደት ሴራን ናይሮቢ ውስጥ አቀንቅነዋል–ኢትዮጵያ በኦሞ ወንዝ ላይ የምታካሂደውን የልማት ስራ የማስረዳት ምክክር አድርገናል የሚል።

ታዲያ "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" አካሄድኩት ባለው በዚሁ ምክክር ላይ ኢትዮጵያ በኦሞ ወንዝ ላይ በምትገነባው ግድብ የተነሳ ኬንያ ውስጥ በሚገኘው ቱርካና ሃይቅ ላይ ሊደርስ ስለሚችለው ተፅዕኖ ከአካባቢው አጋሮችና ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር ባደረገው ውይይት ከፍተኛ የግንዛቤ ክፍተት መኖሩን ተረድቻለሁ ሲል ደስኩሯል።

ታዲያ ይህ የተቋሙ አባባል በዓለማችን እስካሁን ድረስ ወደር ያልገኘለት ዕውቁ የሳይንስ ሊቅ አልበርት አንስታይን በአንድ ወቅት የተናገረውን ብሂል ያስታውሰኛል። እርሱም "እብደት ማለት አንድን ነገር በተመሳሳይ መንገድ ደግሞ ደጋግሞ መሞከርና የተለየ ውጤትን መጠበቅ ነው" የሚለው ትክክለኛ እሳቤን ነው።

ይህ የአንስታይን "የእብድነት" ብያኔ የሚያስረዳን ነገር ቢኖር፣ አንድን ጉዳይ በአሉታዊም ይሁን በአዎንታዊ መልኩ ደጋግመን ሞክረነው ተመሳሳይ ውጤት ሰጥቶን ሲያበቃ፣ እንደገና በሌላ ሙከራ የተለየ ውጤት ለማግኘት መጣር የእብድ ስራ መሆኑን ነው። አባባሉን ጨዋነትን ወደ ተላበሰ ሀገርኛ ቋንቋ ስንመልሰው፣ "ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ አለ" የማለት ያህል ሆኖ እናገኘዋለን።

መቼም ውድ አንባቢዎቼ ይህን አባባል ያነሳሁት በተደጋጋሚ ሙከራ ውጤት ስለሚያስገኙና ስለማያስገኙ ነገሮች ለመተንተን አለመሆኑን እንደምትረዱልኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

የአንስታይንን "የእብደት" ትርጓሜ ለፅሑፌ ማንፀሪያ ይሆንልኝ ዘንድ በመግቢያነት የተጠቀምኩበት ምክንያት፤ ከመሰንበቻው ከስያሜያቸው ጋር ምንም ዓይነት ተፈጥሮአዊ ግንኙነት ከሌላቸውና የራሳቸውን ፖለቲካዊ ግብ ለማሳካት ከተቋቋሙት አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ውስጥ ራሱን "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" በማለት የሚጠራው ተቋም "ግልገል ጊቤ-ሶስት" የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብን አስመልክቶ ልክ እንዳለፉት ጊዜያት በተደጋጋሚ ያወጣው ተደጋጋሚ ሪፖርት ከአባባሉ ጋር ተመሳስሎብኝ ነው።

በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት ይህ ተቋምም ይሁን ሌሎች በተለያዩ ስያሜዎች የሚንቀሳቀሱ ሌሎች አክራሪ ኒዮሊበራል ተቋሞች የአልበርት አንስታይን የ"እብደት" ብያኔን ይጋራሉ።

ምክንያቱም በተያዩ ጊዜያት የሀገራችንን ህዳሴ በፅኑ መሰረት ላይ ለማቆም በልማታዊ መንግስታችን አማካኝነት የሚከናወኑ ልማታዊ ተግባሮችን እንዲሁም "ግልገል ጊቤ-ሶስት" ግድብ ላይ ላይ የቤተክስርቲያን ስዕለት ያለባቸው ይመስል በየሁለትና በየሶስት ወሩ ተደጋጋሚና ተመሳሳይ የሪፖርት ጋጋታን እያወጡ የተለየ ውጤትን ለማግኘት የሚቋምጡ በመሆናቸው ነው።

"የአካባቢ ደህንነት ተቆርቋሪ እና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች" ነን የሚሉ አክራሪ ኒዮ - ሊበራል ኃይሎች ከራሳቸው ስውር የፖለቲካ ፍላጎት በመነሳት በየጊዜው በመንግስት የተሰሩትንና በመሰራት ላይ የሚገኙትን ግድቦች በመኮነን፤ ሀገራችን የምታካሂደውን የልማት ጥረት ለማደናቀፍ ያላደረጉት ጥረት አለመኖሩ ከማናችንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ እናም የአደናቃፊነት ድርሳናቸውን በጥቂቱ የኋሊት መለስ ብለን መመልከት እንችላለን።

በምርጫ 2002 ወቅት ራሳቸውን "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ፣ ሰርቫይቫል ኢንተርናሽል፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ የቱርካና ወዳጆች ማህበር" ... ወዘተ. በተሰኙ ድርጅቶች ፤ የግልገል ግቤ- ሁለትን፣ የተከዜንና የጣና በለስ ግድቦችን በመቃወም ሲያወጧቸው የነበሩት አራምባና ቆቦ የመግለጫ ጋጋታዎች የእነዚህን ኃይሎች ድብቅ ፖለቲካዊ አጀንዳ የሚያሳብቅ ለመሆኑ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል–ምንም እንኳን ሰሚ ጆሮ ባያገኙም፡፡ ከክብሩ የሰው ልጅ ህይወት ይልቅ ለቢራቢሮ ህይወት ቅድሚያ የሚሰጡት እነዚህ በተለያዩ ስያሜዎች ለራሳቸው ፖለቲካዊ ፍላጎት ሲሉ የተደራጁ ተቋሞች፤ ልክ እንደ ሌሎቹ ግድቦች ሁሉ ገና ከግንባታው ጀምሮ እንዲሁም ፕሮጀክቱ ሁለት ሶስተኛው እስከተጠናቀቀበት እስከ አሁኑ ወቅት ድረስ ግልገል ግቤ-ሦስትን የኢትዮጵያ መንግስት እንዳይሰራ የተለያዩ ሰበብ-አስባቦችን በመደርደር ሲቃወሙ ቆይተዋል፡፡

ዛሬ ደግሞ በአዲስ መልክ "ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል" የሚል ያረጀ ያፈጀን ብሂል ይዞ አንድን ጉዳይ በመደጋገም ከሚታወቁት ከእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ጋር በጥምረት የሚሰራው "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" የተሰኘው አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተቋም መሬት ላይ ያሉትን ዕውነታዎች ከመጤፍ ሳይቆጥር የተለመደና እንደ ሐምሌና ነሐሴ ዝናብ የማያባራ የልቦለድ ድርሰቱን በድጋሚ ይዞ ብቅ ብሏል።

ይኸውም ተቋሙ ያለ አንዳች ተጨባጭ ማስረጃ "ጊቤ- ሶስት ቱርካና ሃይቅን ወደ አሮጌ ሃይቅነት ያሸጋግረዋል፣ ግድቡ የኦሞ የቱርካና ሐይቅ 22 በመቶ ዝቅ እንዲል አድርጎ ስነ-ምህዳርን በመጉዳት በእንስሳትና በዕፅዋት ላይ አደጋ ያስከትላል።

የኦሞ ወንዝንም ለመስኖ የመጠቀም ዕድሉን ይቀንሰዋል፣ ይህም ግማሽ ሚለዩን በሚጠጉ የአካባባቢው ነዋሪዎች ላይ ከባድ ተፅዕኖ ያሳርፉል። እንዲሁም መንግስት የአካባቢውን ነዋሪዎች በግዳጅ እያሰፈረ ነው፤ የግድቡ ግንባታ ድንበር ተሻጋሪ ውጥረቶችን ይቀሰቅሳል" የሚሉ ውሸትን ብቻ ያዘለ ጥንቆላ መሳይ ሪፖርቱን ይፋ አድርጓል።

ታዲያ ለዚህ የተቋሙ ተደጋጋሚና ፖለቲካዊ ግብ ያጠላበት ሪፖርት የሀገሬ ዕድገት ይመለከተኛል እንደሚል እንደ ማንኛውም ዜጋ አግባብ ያለው ምላሽ መስጠት ተገቢ

ነው ብዬ አምናለሁ—"አካፋን አካፋ" ማለት ከማንኛውም ሀገር ወዳድ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ነውና።

ሆኖም ለ"ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" ልቦለዳዊ ቅመራ ሪፖርት ምላሽ ከመስጠቴ በፊት፤ አንድ ሀገር እምቅ የተፈጥሮ ፀጋዎቿን መጠቀሟ ለዕድገቷ ያለው ፋይዳን እንዲሁም ግልገል ጊቤ ሶስት በቱርካና ሃይቅ አካባቢ ለሚኖሩ ህዝቦች ያለውን ጠቀሜታ መመልከት ጠቃሚ ነው።

ምክንያቱም ከእነዚህ አንኳር ጉዳዩች አኳያ የምናነሳቸው ነጥቦች "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ"ም ይሁን ሌሎች "ለምን ከእኛ ፈቃድና ርዕዩተ-ዓለም ውጪ ታድጋላችሁ" የሚሉ ሌሎች አክራሪ ኒዩ-ሊበራሎች ከፈለጉ ሃቁን እንዲያውቁ ብሎም የልቦለድ ድርሰታቸውን በበቂ ሁኔታ ለመገንዘብ ስለሚያስችለን ነው።

እንደሚታወቀው የየትኛውም ሀገር ህዝብ የተፈጥሮ ሀብቶቹን ለልማቱ አጋዥ በሆነ መልኩ ካልተጠቀመባቸው፤ ባለንበት የግሎባላይዜሽን ዘመን ተወዳዳሪ ሆኖ በፈጣን ሁኔታ ለማደግ ያለው ተስፋ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ከሚታይ የብርሃን ጭላንጭል የዘለለ ሊሆን አይችልም፡፡

በመሆኑም በዕድገት ግስጋሴው ውስጥ እምቅ ተፈጥሮአዊ ፀጋዎችን ከሚፈለገው ልማት ጋር እያስተሳሰረ ጥቅም ላይ ማዋሉ፤ በግብነት የሚታቀዱ ማናቸውንም ሀገራዊ ውጥኖች ዕውን ለማድረግ ያለው ሚና የማይተካ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡

ይህን ዕውነታ በውል የተገነዘበው የሀገራችን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት የጀመረውን ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ለማስቀጠል ፤ የተፈጥሮ ሀብታችንን በተገቢው መንገድ መጠቀም ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

እነዚህ ሀብቶች የሀገራችንን ህዳሴ በጽኑ መሰረት ላይ ለመገንባት በሚደረገው ልማታዊ ርብርብ የላቀ ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከተፈጥሮ ስጦታዎችን ውስጥ ደግሞ ውኃ አንዱ ነው፡፡

እርግጥም የውኃ ሀብታችንን በተገቢው ሁኔታ ብንጠቀምበት 45 ሺህ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት እንችላለን፡፡ ይህም ከኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ቀጥሎ በአፍሪካ ውስጥ ትልቁን ኃይል የምናመነጭ ሀገር እንድንሆን ከማስቻሉም ባሻገር፤ ወደ ዕድገት ጎዳና ለመሸጋገር የምናደርገውን ጥረት አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ እንድናከናውን ያደርገናል፡፡ ታዲያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት መንግስት ከዚህ ዕውነታ ተነስቶ በወሰዳቸው ርምጃዎች በርካታ የከተማና የገጠር ቀበሌዎችን የብርሃን ጸዳል ሊያላብሳቸው ችሏል፡፡

ይህ ልማታዊ ተግባሩም ህዝቡ በራሱ ሃብት ተጠቃሚ መሆን መጀመሩን የሚያረጋግጥ ዕውነታ ለመሆኑ መስካሪ የሚያሻው ጉዳይ አይመስለኝም። እናም እነ "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" ህዝባችሁ ለምን እኛ ዕውቅና ሳንሰጠው በራሱ መንገድ ያድጋል?፣ ለምንስ ከተፈጥሮ ፀጋዎቹ ተጠቃሚ ይሆናል? በማለት ያለ ተጨባጭ ማስረጃ የራሳቸውን ርዕዮተ-ዓለም ለማስኬድ መሞከራቸው ግባቸው ፖለቲካዊ እንጂ ከህዝቦች ተጠቃሚነት ጋር የሚያገናኘው አንዳች ነገር የሌለ መሆኑን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው።

እንደሚታወቀው "ግልገል ጊቤ- ሶስት" 1870 ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም አለው። ፕሮጀክቱም በአሁኑ ወቅት ሁለት ሶስተኛው ተጠናቅቋል። እርግጥ "ጊቤ - ሦስት" ህዳሴያችንን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የተነደፈው የአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንድ አካል ነው፡፡ ይህም ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ጋር ተዳምሮ ሌላኛው የህዳሴያችን መደላድል ብርሃን ፈንጣቂ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

በኦሞ ወንዝ ላይ የሚገነባው ይህ ግድብ፣ በኢትዮጵያና በኬንያ መንግስታት የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ባደረገ መልኩ በመገንባት ላይ የሚገኝ ፕሮጀክት ነው፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያዊያኑ ሙርሲዎችና ኛንጋቶሞች የሚገኙበት ኦሞ ወንዝ ለኬንያው የቱርካና ሐይቅ ገባር ቢሆንም፤ በወንዙ ላይ የሚገነባው "ጊቤ- ሦሰት" በሐይቁም ይሁን በአካባቢው በሚኖሩ "ቱርካናዎች" ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ተፅዕኖ የለም፡፡

ከዚህ ይልቅ በአካባቢው ለሚገኙ ህዝቦችና ለቱርካና ሐይቅ የጎላ ጠቀሜታ ያለው እንዲሁም ቀደም ሲል የነበረውን የሁለቱን ሀገራት የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ይበልጥ የሚያጠናክረው መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ ታዲያ ጥቅል ዕውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፤ አክራሪ ኒዮ - ሊበራሉ ተቋም በተደጋጋሚ የግድቡን ግንባታ ለምን ይቃወማል? የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ይሁንና ለጥያቄው ምላሽ ሩቅ መሄድ አያሻንም፡፡ ምክንያቱም በግልጽ የሚታዩ ሦስት ምክንያቶችን ብቻ መጥቀስ በቂ ስለሆነ ነው፡፡

በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት፤ "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" ከሌሎች የትግል አጋሮቹ ጋር ጊቤ- ሦስትን የሚቃወምትና የተቀናጀ ዘመቻ የሚያካሂድበት ዋነኛዎቹ ምክንያቶች፤ የአፍሪካዊያንን ልማት (በተለይም በራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ማደግ የጀመሩትን ህዝቦች ) ለማደናቀፍ፣ በቢራቢሮ ህይወት ናፋቂነት ሳቢያ ጥቅማቸውን ላለማጣት እና አፍሪካዊ የኢኮኖሚ ትስስርን ለማዳከም ከታለሙ ድብቅ አጀንዳዎች የመነጩ ናቸው፡፡ ይሁንና የእነዚህን ኃይሎች መሰረተ-ቢስ አሉባልታዎችን ተራ በተራ መመልከት፤ ሃቁን በማያሻማ ሁኔታ እንድንረዳ ያግዙናል፡፡

እነ "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" አፍሪካ በራሷ የልማት መንገድና የፖለቲካ ዘይቤ እንድታድግ የሚፈቅዱ ኃይሎች አይደሉም፡፡ ይህ እሳቤያቸውም በየትኛውም አፍሪካዊ ሀገር ላይ ያለምንም መሸራረፍ የሚሰራ ነው፡፡

ታዲያ ይህን "የመከነ ፖለቲካቸውን" ተፈጻሚ ለማድረግ ለራሳቸው "ለትርፍ ያልተቋቋመ" የሚል ስያሜ በመስጠት በተለያዩ ምግባረ ሰናይና ሲቪክ ማህበራት የሽፋን ስም ይደራጁና የሀገራቱን ልማት ለማደናቀፍ የማይቧጥጡት ዳገት፣ የማይቆፍሩት ጉድጓድ የለም፡፡

ይህን ለመተግበርም በየሀገራቱ ውስጥትላልቅ ተቋማትን ከመጠቀም ጀምሮ የቀለም አብዮትን እስከ ማቀጣጠል ድረስ ይደርሳሉ፡፡ በእኛ ሀገር ነባራዊ ሁኔታ ግን የቀለም አብዮት የሚካሄድበት ምንም ዓይነት ተጫባጭ ምህዳር ባለመኖሩ፤ የቁራ ጩኸታቸውን የሚሰማቸው ሲያጡ አማራጫቸውን "ውሸትን ብንደጋግም እውነት

ይመስልልናል" የሚል አሮጌ ይትብሃልን እየተከተሉ መሆናቸውን ለመገንዘብ አይከብድም፡፡

ምንም እንኳን ጽንፈኛ ተቋሞቹ "... የግልገል ጊቤ - ሦስት ፕሮጀክት በአካባቢው ህዝብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳርፋል" እያሉ በየጊዜው ሊቀሰቅሱ ቢሞክሩም፤ ተጨባጭ ዕውነታው ግን ይህ አይደለም፡፡ የግድቡ መንገባት ህዝባዊም ይሁን ስነ-ምህዳራዊ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ለመግለፅ ጠቀሜታው ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡

ይሁንና ጥቂት ዋና ዋና አብነቶችን ለመጥቀስ ያህል የግድቡ መገንባት፤ የአካባቢው ህዝብ ከከብት እርባታ በተጨማሪ በአሳ ማስገርና በመስኖ ልማት እንዲጠቀም የሚያስችል ከመሆኑም በላይ፤ እጅግ ኋላ ቀር በሆነው በዚያ አካባቢ ትምህርት ቤት ፣ ሆስፒታል፣ መንገድና ኢንቨስትመንትን የመሳሰሉ የመሰረተ - ልማትና የንግድ ስራዎች እንዲካሄዱ ዕድል በመፍጠር ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፤ ለዘመናት የብርሃን ጭላንጭል አይቶ የማያውቀው የአካባቢው ህዝብ የኤሌክትሪክ ኃይል ሰለሚያገኝ በአኗኗር ዘይቤው ላይ ለውጥ ያመጣል፤ ቀደም ሲል በውኃ ሙላት ይጥለቀለቁ የነበሩት ህዝቦችን ህይወት ለመታደግም የግድቡ መገንባት ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

ሌሎቹ ቀርተው እነዚህ በጣት የሚቆጠሩ ጠቀሜታዎች ብቻ የእነ "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" የፈጠራ "አሉታዊ ተፅዕኖን" እርቃኑን የሚያስቀሩት ናቸው፡፡ ታዲያ የጥቅሞቹ ተቋዳሾች በወንዙ አካባቢ የሚገኙት ኢትዮጵያዊያኑ ኛንጋቶሞችና ሙርሲዎች ብቻ አይደሉም፡፡ ኬኒያዊያኑ ቱርካናዎችም ከግድቡ መገንባት ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ይህም ግድቡ በአካባቢው የሚገኙትን ሁሉንም ህዝቦች ወደ ተሻለ ህይወትና የልማት አቅጣጫ የሚወስድ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ሆኖም እዚህ ላይ 'ሃቁ ግድቡ ህዝቦችን በልማት ተጠቃሚ እንደሚያደርግ መሆኑ እየታወቀ፤ "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" እና መሰሎቹ ለምን ይዋሻሉ?' የሚል ጥያቄ ስናነሳ፣ ምላሹ ቀደም ሲል ወደጠቀስኩት ወደ መጀመሪያው ምክንያታቸው

ይወስደናል፡፡ ይኸውም እነዚህ ኃይሎች ከኒዮ- ሊበራል አስተሳሰብ ውጪ በራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ለማደግ ደፋ ቀና የሚሉ ሀገሮችን ለመድፈቅ የሚያደርጉት ትዕይንት መሆኑ ነው፡፡

በሚያስገርም ሁኔታ ለህዝቦች ተቆርቋሪ በመምሰል መልሰው የህዝቦችን ልማታዊ እመርታ በፈጠራው ወሬ ለማኮላሸት የሚሯሯጡት አክራሪዎቹ ኃይሎች፤ "...የግድቡ ግንባታ የቱርካና ሐይቅን ህልውና አደጋ ላይ ጥሎ ወደ አሮጌ ሐይቅነት ይቀይረዋል፣ የእንስሳትንና ዕጽዋቶችን ጥናት ለማካሄድ ስለሚያስቸግር ኢትዮጵያ ለሃይቁ ደህንነት ማሰብ አለባት..." በማለት ያቀረቡት እምክንዮ ውኃ አይቋጥርም። ይህ ምልከታቸውም በቢ.ራቢ.ሮ ህይወት ናፋቂነት ሳቢያ ጥቅማቸውን ላለማጣት ወደሚያደርጉት የዘመቻው ሁለተኛ ምክንያት የሚወስደን ነው፡፡

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት እነዚህ ኃይሎች አፍሪካዊያን እንዳያድጉና የምንጊዜም ተመጽዋች ሆነው እንዲኖሩ የሚሹ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት አፍሪካ ውስጥ ያሉ አርብቶ አደሮች በተፈጥሮ ፀጋዎቻቸው እንዳይለሙ ከማድረግ ባሻገር፤ የተለያዩ የፈጠራም ምክንያቶችን በመደርደር ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ህይወት ግዑዝ ከሆነው ሃይቅ እንዲሁም ከእንስሳትና የዕፅዋት አሳንሰው ይመለከቱታል፡፡

ለዚህም ነው የአርብቶ አደሩን ብሎም የአጠቃላይ የሀገራችንን ህዳሴ ለማሳለጥ የሚገነባውን "ግቤ - ሦስትን"፤ ከጥቃቅን እንስሳትና ዕፅዋት ጋር የግድ በማቆራኘት "ለእነ ቢ.ራቢ.ሮ" ግንባር ቀደም አቀንቃኝ በመሆን ጥቅማቸው እንዳይነካ የሚጥሩት፡፡

ዳሩ ግን እነርሱ ያሻቸውን ቢሉም፤ ዕውነታው በፍጹም ከፈጠራ ታሪኮቻቸው ጋር የተገናኘ አይደለም፡፡ "ጊቤ - ሦስት" በቱርካና ሐይቅ ላይም ይሁን በአካባቢው ሥነ - ምህዳር ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ጉዳት የለም፡፡

ከዚህ ይልቅ የግድቡ መሰራት በየጊዜው በመዋዥቅ የሚታወቀውን የቱርካና ሐይቅ ፍሰት ወጥነት እንዲኖረው እንዲሁም ትነቱ እንዲቀነስና የውኃው መጠንም እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

ይሁንና “ኢንተርናሽናል ሪቨርስ” ከዚህ ሃቅ ተገላቢጦሽ በሆነ ሁኔታ ያለሃፍረት “ዓይኔን ግንባር ያድርገው” በማለት የግድቡ መገንባት የቱርካናን ሐይቅ ውኃን በ22 ሜትር እንደሚቀንሰው ይቦተልካል፡፡

ነገር ግን ይህ የፈጠራ ወሬ ከእውነት የራቀ መሆኑን የአፍሪካ ልማት ባንክ ፣ ከስምንት ሀገራት የተውጣጡ የለጋሽ ሀገራት ዲፕሎማቶች እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት /ተመድ/ የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም እ.ኤ.አ. የፌብሩዋሪ 2012 ሪፖርት ብሎም ግድቡን እንዲጎበኙና የቅኝት ስራ እንዲያካሂዱ የተጋበዙት የኬንያ መንግስት ልዑካን ቡድን አባላት ውድቅ አድርገውታል፡፡

የአፍሪካ ልማት ባንክ የቅርብ ጊዜ ሪፖርት፤ “ጊቤ - ሦስት” በኢትዮጵያም ይሁን በኬንያ የግድቡ አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦችንም ይሁን የተፈጠሮ ሃብትን እንደማይጎዳ አረጋግጧል፡፡ ግድቡን ለመጎብኘት በቦታው የተገኘውና ለበርካታ ቀናት ጉዳዩን ሲያጠና የነበረው የስምንት ለጋሽ ሀገራት አምባሳደሮች ቡድንም የእነ “ኢንተርናሽናል ሪቨርስ”ን የማያባራ ልቦለዳዊ ድርሰት “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” መሆኑን አጋልጧል።

ከዚህ በተጨማሪም በተመድ የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም እ.ኤ.አ. የፌብሩዋሪ 2012 ሪፖርቱ እንዳለው፤ በአካባቢው የሚገኙ ሰፋሪዎችን አነጋግሮ ምንም ዓይነት የግዳጅ ሰፈራ አለመከናወኑን እንደተረዳ ይፋ አድርጓል። ግድቡን በተመለከተም የተለየ የአየር ፀባይ ለውጥ እስካልተከሰተ ድረስ የአሞ ወንዝ ውሃ 80 በመቶው ወደ ቱርካና ሃይቅ መፍሰሱን እንደሚቀጥል ገልጿል።

የዝናብ መጠኑ ሁኔታ የሚያሰጋ ከሆነ ሃይቁ በየ7 ወራት ጊዜ ውስጥ በ2 ሜትር ዝቅ የማለት ሁኔታ ሊያሳይ እንደሚችልም ጠቁሟል። ይሁንና የዝናቡ መጠን ወጥ ከሆነ በሃይቁ ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ እንደማይኖርም አትቷል።

እንግዲህ ከዚህ ዕውነታ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር “ኢንተርናሽናል ሪቨስር” ያቀረበው ሪፖርት ተረት-ተረት መሆኑን ነው። ምክንያቱም በግዳጅ ሰፈሩ የተባሉት ዜጎች ጉዳዩን ይህ ቅጥፈት ነው ማለታቸው፤ ከዚህ በተጨማሪም የቱርካና ሃይቅ መጠን ሊቀንስ አሊያም ሊጨምር የሚችለው ከተፈጥሮ የአየር ሁኔታ ጋር በተያያዘ እንዲሁም በአካባቢው በሚጥለው ዝናብ ላይ የሚመሰረት መሆኑን በገለልተኛ ቡድን በመታወቁ ነው።

ይህም የአክራሪ ቡድኑ ውትወታ ከግልገል ጊቤ ሶስት ግንባታ ጋር የሚያያይዘው አንዳችም ነገር የሌለ መሆኑን ያመላክታል። ይልቁንም ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት የግድቡ ግንባታ እውን መሆን ለሃይቁም ይሁን ለኦሞ ወንዝ ብሎም ለአካባቢው ማህበረሰብ ጠቀሜታው የጎላ ያረጋግጣል።

የኬንያ ልዑካን ቡድን አባላትም ከዛሬ አንድ ዓመት ተኩል በፊት ባደረጉት ምልከታ የበኩሉላቸውን አስተያየት ሰጥተው ነበር። ይኸውም በወቅቱ የግድቡ መገንባት ለቱርካና ሐይቅ ጠቃሚ እንደሆነና ሀገራቸው ያለባትን የኃይል እጥረትንም በአጭር ጊዜ ውስጥ በመቅረፍ ህዝባቸውን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ እምነታቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ታዲያ ሌላው ቢቀር ከዚህ ጉዳዩ ከሚመለከተው ቡድን ውጪ ከቶ ማን ትክክለኛ እማኝና ምስክር ሊሆን ይችላል?...

እርግጥ የእነ “ኢንተርናሽናል ሪቨርስ” ምንም ዓይነት ትክክለኛ ምስክርነትን የሚሰሙ አይደሉም። ከእነርሱ ርዕዮተ-ዓለም ውጪ ዕድገቱን በማፋጠን ላይ የሚገኝ ሀገር ትክክል ነገር ቢሰራም ተቀባይነት የለውም። እንዲያውም ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ዓለም አቀፍ ታላላቅ ተቋማትን ሳይቀር ከማሳሳት ወደ ኋላ አይሉም።

ለዚህም የዛሬ ዓመት ገደማ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጊቤ ሶስት በአካባቢው ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ እሲጣራ ድረስ ግንባታው እንዲቆም እንዲጠይቅ ማድረጋቸው አይዘነጋም።

ምንም እንኳን ድርጅቱ የማታ ማታ አምና ላይ ቀደም ሲል በጠቀስኩት በአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም መስሪያ ቤቱ አማካኝነት የግድቡ ግንባታ በቱርካና ሃይቅና በኦሞ

ወንዝ እንዲሁም በአካባቢው በሚገኙ የኢትዮጵያና በኬንያ ዜጎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሳድር መሆኑን ባደረገው ጥናት ቢያረጋግጥም።

ውድ አንባቢዎቼ! እነዚህ ኃይሎች በዚህ የለየለት ቅጥፈታቸው ስለ ሃይቅ፣ ዕፅዋትና እንስሳት ብሎም ስለ አካባቢው ሰዎች "ጉዳት" የሚያነበንቡት፤ ከኬንያና ከኢትዮጵያ መንግስታት በላይ ለህዝቦች ተቆርቋሪና ለሥነ- ምህዳር አሳቢ ሆነው እንዳይመስላችሁ፡፡ ይልቁንም በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ላይ እንዲህ ዓይነቱን የማደናገሪያ ሪፖርቶችን ሳያሰለሱ የሚያወጡት፤ ከራሳቸው ህልውና አንጻር የሀገራቱን ዕድገት የጎሪጥ ስለሚመለከቱት ነው፡፡ ግና እንዴት? ... ነገሩ ወዲህ ነው።

እንደሚታወቀው "የወንዞች ጉዳይ ይመለከተናል፣ ለህዝቦች ሰብዓዊ መብት እንሟገታለን፣ ግጭቶችን እንፈታለን...ወዘተ" በሚል የሽፋን ስም ተደራጁት እንደ ኢንተርናሽናል ሪቨርስ፣ ሂዮማን ራይትስ ዎች፣ ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ተቋማት፤ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ዕድገታቸውን በተገቢው ደረጃ ካረጋገጡ እነርሱ በሽፋንነት የተደራጁበት ሚናቸው ተፈላጊ እንደማይሆን ጠንቅቀው ይገነዘቡታል፡፡

ምክንያቱም ሀገራቱ የተፈጥሮ ፀጋዎቻቸውን በተገቢ ሁኔታ ተጠቅመው የዕድገት ማማን በከፍተኛ ደረጃ መቆናጠጥ ከጀመሩ፤ እንከራከርለታለን የሚሉት ሰብዓዊ መብት፣ እንፈታቸዋለን የሚሏቸው ግጭቶች ወዘተ. ከዕድገቱ ጋር ተያይዘው ችግርነታቸው ስለሚያበቃ፤ የተከናነቡት የውሸት ጭምብል መገፈፉ ስለማይቀር ነው፡፡

ይህም ከድብቅ የፖለቲካ አጀንዳቸው ባሻገር፤ በሰብዓዊ መብትና በግጭቶች ሰበብ ቀደም ሲል ወደ ኪሳቸው ይገባ የነበረው ረብጣ ዶላር እንዳይኖር ስለሚያደርግ ጥቅማቸውን ክፉኛ ያጎዳዋል፡፡

ታዲያ ይህ ጥቅማቸው እንዳይቀር ከሰው ልጅ ክቡር ህይወት ይልቅ ለቢራቢሮና ለግዑዛን ፍጥረታት ህልውና በማላዘን ሀገራቱ ዕድገታቸውን እንዳያሳልጡ የልማት ጋሬጣ በመሆን ፊት ለፊታቸው ይገተራሉ፡፡

ይህን ሃቅ "ከጊቤ - ሦስት" አኳያ ስንመለከተው፤ በግድቡ መሰራት ሳቢያ ኢትዮጵያዊኑ ኛንጋቶሞችና ሙርሲዎች እንዲሁም ኬንያዊያኑ ቱርካናዎች ከኩራዝ ኑሮ ወጥተው የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ መሆናቸው አይቀርም፡፡

ይህም የአካባቢው ህዝቦች በመሰረተ - ልማትና በሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶች ሳቢያ ዓይናቸውን በመክፈት የአኗኗር ዘይቤያቸውን እንዲቀይሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ህይወትን ከዚህ በፊት ከነበረው በተለየ ሁኔታም መምራት ይጀምራሉ፡፡

የወንዞችንና የሰብዓዊ መብት ጥቅምን እንዲሁም የግጭት አላስፈላጊነትን ስለሚገነዘቡም ቀደም ሲል በግጦሽና በውኃ ምክንያት ከሚጋጩቸው ህዝቦች ጋር በሠላም ተከባብረው ይኖራሉ፡፡ ታዲያ አንድ ህዝብ ከዕድገት ጋር ተያይዞ በሚፈጥረው ሚዛናዊ እሳቤ ስለ የተፈጥሮ ፀጋ ጠቀሜታ፣ ስለ ሰብዓዊ መብትም ይሁን ስለ ግጭት አፈታት በቂ ግንዛቤ ከያዘ ፤ በእነዚህ ጉዳዩች ላይ እንሟገታለን የሚሉ ድርጅቶች አያስፈልጉም፡፡ ከልማቱ ጋር በሚዳብር ንቃተ - ህሊና የተመቻቸ አካባቢና የቅርስ ጥበቃ አስተሳሰብ መጎልበቱ ስለማይቀር፤ የአካባቢ ተንከባካቢ ድርጅትም ተፈላጊነት የለውም፡፡

በዚህም ሳቢያ " የጊቤ - ሦስት " መገንባት አደጋው ከአካባቢው ህዝቦችና ስነ-ምህዳር ይልቅ ለአክራሪ ኒዮ - ሊበራል ተቋሞች ይሆናል ማለት ነው፡፡ ለዚህም ነው እነዚህ ሃይሎች የግድቡን ግንባታ በየወቅቱ በበዘመቻ መልክ ከማውገዝ ባለፈ፤ ተረኛ ሪፖርት አውጪው "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" "የአብዬን ወደ እምዬ" እንዲሉ በሌለ ነባራዊ ሁኔታ "ግድቡ ድንበር ተሻጋሪ ውጥረትና ግጭት ሊቀሰቅስ ይችላል" የሚል አጭር ልቦለድ የቀመረው ፡፡ ነገሩ "የዳቦ" ጉዳይ ነውና።

ግና ወደፊት በግድቡ ሳቢያ ውጥረት እንዴት ሊከሰት እንደሚችል ሊነግረን ይገባል። ምክንያቱም የኬንያንና የኢትዮጵያን ህዝቦች ተጠቃሚ የሚያደርገው ጊቤ ሶስት የውጥረትና የግጭት መነሻ ሊሆን ስለማይችል ነው።

ምናልባትም አክራሪው ኒዩ-ሊበራል ሃይልም ይሁን መሰሎቹ እንጀራቸውን ላለማጣት በጣልቃ ገብነት ወደፊት በቀጣናው ውስጥ ውጥረት እንዲነግስ የሚሰሩ ከሆነም ማወቁ አይከፋም።

ምክንያቱም ከልምድ እንደሚታወቀው አክራሪ ኒዩ-ለበራል ሃይሎች በሀገራት ጉዳዩች ውስጥ ጣልቃ እየገቡ የቀለም አብዩት በማቀጣጠል እንዲሁም ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ አስቀድመው ሪፖርት በማውጣት ማናቸውንም እኩይ ሴራ ከመፈፀም ወደ ኋላ የሚሉ ስላልሆነ ነው።

እናም ሃሳባቸው ከእነዚህ ተግባራት ውስጥ አንዱ ከሆነ በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነትም ይሁን ሴራውን የሚያስተናግድ ምህዳር የሌለ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ያም ሆነ ይህ ግን፤ ኢትዮጵያ የጀመረችውን የዕድገት ጉዞ ይበልጥ እንዲፋጠን በተፈጥሮ ሀብቶቿ ለመጠቀም የማንንም ፈቃድና ይሁንታ የማትጠይቅ ሀገር መሆኗን "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ" በሚገባ ሊገነዘበው ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር ሌላኛው የህዳሴያችን መደላድል ፈጣሪ የሆነውን "ግቤ - ሦስትን" ለልማት ከማዋል ተግባሯ በውሸት መግለጫዎች ጋጋታ ወደ ኋላ የምትልበት አንዳች ምክንያት የሌለ መሆኑን ማወቁ በጄ ነው፡፡

እናም አልበርት አንስታይን እንዳለው፤ አንድን ጉዳይ በተመሳሳይ መንገድ ደግሞ ደጋግሞ በመሞከር የተለየ ውጤት ለማግኘት መጠበቅ እብድነት መሆኑን "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ"ም ይሁን ወረፈኛ አጋሮቹ መረዳት አለባቸው። አዎ! ጊቤ-ሶስት ላይ በየተራ እየደጋገሙ ሪፖርት በሚል የተሰለቸ ዘዴ 'ምናልባት ኢትዮጵያ ግድቡን ታቆም ይሆናል' የሚል የተለየ ውጤትን መጠበቅ እብድነት ነው— ለዚያውም በዕድገታችንና በብሔራዊ ጥቅማችን ላይ ያነጣጠረ እብድነት። ያም ሆነ ይህ ግን "ኢንተርናሽናል ሪቨርስ"ም ሆነ አጫፋሪዎቹ ሀገራችን በኦሞ ወንዝ ላይ በምታካሂደው የግድብ ግንባታ ላይ የሚያመጡት አንዳችም ለውጥ የለም—ግድቡ ሲጠናቀቅ

የኬንያንም ሆነ የኢትዮጵያን ህዝቦች ተጠቃሚ ማድረጉ የሁለቱም ሀገራት ዜጎች ጠንቅቀው ስለሚያውቁት ነው። ታዲያ ተቋሙ ላይሳካለት ባይደክም ምናለበት?...